በኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን
ETHIOPIAN CUSTOMS AUTHORITHY
የአዲስ አበባ ቃሊቲ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት
ADDIS ABABA KALITY CUSTOMS BRANCH OFFICE
የውስጥ ማስታወሻ /INTER OFFICE MEMO/

ቁጥር: ስ/አ/ጽ/ቤት 258/09
ቀን: 26/04/09 ዓ.ም

ለ:- ሁሉም ሥራ ሂደቶች
ለ:- ገላን ተርሚናል ጉምሩክ ማስተባበሪያ
ለ:- ጉምሩ ጉዳዮች አቤቱታ አጣሪ
ለ:- ውስጥ ኦዲት ቡድን
ለ:- ስነ-ምግባር መከታተያ ቡድን
ለ:- ሴቶ ወጣቶች ጉዳይ
ለ:- ሰው ሀብት ስራ አመራር ቡድን

ከ:- ሥራ አስኪያጅ ጽ/ቤት
<u>አ/አ/ቃ/ጉ/ቅ/ጽ/ቤት</u>፣

የጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤቶች ድጋፍና ክትትል ዳይሬክቶሬት በደብዳቤ ቁጥር 3.3.1/430/09 በቀን 27/04/09 በቁጥር መ240-711/5 ታህሳስ 20 ቀን 2009 ዓ.ም ለቅ/ጽ/ቤታችን በጻፈው መሠረት የጠቅላይ ሚኒስስት ጽ/ቤት በቁጥር 02.1.35/619 የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር የኢንቨስትመንት በተፃፈ ደብዳቤ ጥቅምት 21 ቀን 2009 ዓ.ም ከቀረጥ ነፃ እንዳይገባ የተጻፈውን "የእገዳ ደብዳቤ" የተነሳ መሆኑ ፕሮጀክቶች የአርማታ እና ስታፋ ብረቶች <u>ውሳኔ የተነሳ መሆኑ</u> ተገልጾልናል።

በዚህ መሠረት ከቀረጥና ታክስ ነፃ እንዳይገቡ የተወሰነው የአርማታ ብረት እና ስታፋ ብረቶች ውሳኔ የተነሳ መሆኑ ታውቆ ተገቢው አገልግሎት እንዲሰጥ እያሳሰብኩ፤ የተላከውን 2 ገጽ ኮፒና 1 ገጽ ደብዳቤ ከዚህ መሸኛ ደብዳቤ ጋር <u>ታውቆ</u> አባሪ አድርገን የላክን መሆኑን እገልጻለሁ።

ከሰላምታ ጋር

<u>ግልባጭ</u>:-

- ለም/ሥራ አስኪያጅ /የጉምሩክ ጉዳዮች/
- ለም/ሥራ አስኪያጅ /ሞደርናይዜሽንና ኮርፖሬት ዘርፍ/ (ያለአባሪ)

<u>አ.አ ቃሊቲ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት</u>

65 ለ/ገ

ኦሀ 1

46

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን
THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA
ETHIOPIAN REVENUES AND CUSTOMS AUTHORITY

ቁጥር Ref. No 3-3-1/4130/09
ቀን Date 27 ታህሳሰ 2009

ለጉምሩክ ሥነስርዓት ለሚፈጸምባቸዉ ቅ/ጽ/ቤት
በያሉበት

የጠቅላይ ሚኒስትር ጽ/ቤት ታህሳስ 20 ቀን 2009 ዓ/ም በቁጥር መ240-711/5 በተፃፈ ደብዳቤ ጥቅምት 21 ቀን 2009 ዓ/ም በቁጥር 02.1.35/619 የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች የአርማታ እና ስታፍ ብረቶች ከ ቀረጥ ነፃ እንዳይገባ የተጻፋውን "የእገዳ ደብዳቤ" በ ዚህ ደብዳቤ የተነሳ መሆኑን እና ለ ወደፊቱም የኤክስፖርተ አስተባባሪ ኮሚቴ ውሳኔም ሆነ አቅጣጫ ለ አስፈፃሚ መ/ቤቶች የሚተላለፈው በ ጠቅላይ ሚኒስትር ጽ/ቤት በኩል ብቻ መሆኑን ያሳወቀበትን 2 ገጽ ደብዳቤ ለተገቢው አፈፃፀም አባሪ አድርገን ልከናል፡፡

ከሠላምታ ጋር

ማርታ ስዩም
የጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤቶች ድጋፍና
ክትትል ቡድን አስተባባሪ

ግልባጭ፤

- ለጉምሩክ ፕሮግራም ልማትና ድጋፍ ሥራዎች ዘርፍ
- ለጉምሩክ ጉዳይ ቅ/ጽ/ቤቶች ድጋፍና ክትትል ዳይሬክቶሬት
  ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን

04/05/09



ስልክ ቁ / Tel. 011 662 98 00
ፋክስ / Fax: 011 662 99 06
ኢሜል / Email: erca@ethionet.et
ድረ ገጽ / Website: www.erca.gov.et
ፖ.ሣ.ቁ / P.O.Box: 2559
አዲስ አበባ -ኢትዮጵያ

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ**
**የጠቅላይ ሚኒስትር ጽ/ቤት**
***THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA***
***OFFICE OF THE PRIME MINISTER***

ቀን 20 ታህሳስ 2009
*Date*
ቁጥር 00240-711/5
*Ref. No.*

ለኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን
ለኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን
<u>አዲስ አበባ</u>

ጉዳዩ:- <u>የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር በአርማታ እና በስታፋ ብረቶች ላይ ያስተላለፈውን ‹‹ዕገዳ›› ስለማንሳት</u>

የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን ታህሳስ 5 ቀን 2009 በጻፈው ደብዳቤ የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ጥቅምት 21 ቀን 2009 ዓ.ም በቁጥር 02.1.35/619 ባድራሻ ለገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር፣ ለንግድ ሚኒስቴር፣ ለገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን፣ ለኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ እና ለኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን በግልባጭ ለብረታብረት ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት እና ለመሠረታዊ ማህበሩ በጻፈው ደብዳቤ የብሔራዊ ኤክስፖርት አስተባባሪ ኮሚቴ መስከረም 19 ቀን 2009 ዓ.ም. አቅጣጫ የሰጠ መሆኑን በመግለጽ ‹‹ በአሁኑ ጊዜ የአርማታ እና ስታፋ ብረቶችን አገር ውስጥ የማምረት በቂ አቅም የተገነባ ስለሆነ ከቀረጥና ታክስ ነጻ ከውጭ የማስገባት ፈቃድ በኮሚሽኑ እንዳይሰጥ›› በሚል ያስታወቀው በመሆኑ፣ በርካታ የመንግስት፣ የአገር ውስጥና የውጭ ኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች የአርማታ ብረት ከውጭ አገር አስመጥተው የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን አጽድቆላቸው የገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣንን ሲጠይቁ ባለሥልጣኑ ‹‹የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር አግዶታል›› በሚል በሕግ መሠረት የጸደቀን መብት በመከልከሉ ፕሮጀክቶቹ ለከፍተኛ የዲመሬጅ ወጪ በማድረግ ላይ መሆናቸውን ጠቅሶ በህጉ መሠረት አፋጣኝ መፍትሄ እንዲሰጣቸው አቅጣጫ እንዲሰጥበት ጠይቋል።

.../

ስልክ 011-1-22-67-67 *Tel.*
ፋክስ 22 62 92 *Fax*
ፖ.ሣ.ቁ 1268 *P.O.Box*
አዲስ አበባ ኢትዮጵያ *Addis Ababa-Ethiopia*

ስለሆነም ጥቅምት 21 ቀን 2009 ዓ.ም. በቁጥር 02.1.35/619 ከኢንዱስትሪ ሚኒስቴር የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች የአርማታ እና ስታፋ ብረቶች ከቀረጥ ነጻ እንዳይገባ የተጻፈው ‹‹የዕገዳ ደብዳቤ›› በዚህ ደብዳቤ የተነሳ መሆኑን እየገለጽን፣ ከአፈጻጸም ጋር የሚታዩ ችግሮችን ኮሚሽኑ እና ሌሎች አግባብነት ያላቸው አካላት ተገቢ ክትትልና ቁጥጥር እንዲያደርጉ እንዲሁም የሕግ ማሻሻያ የሚያስፈልግ ከሆነ ኮሚሽኑ የባለድርሻ አካላትን በማሳተፍ ጥናት አድርጎ ለኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ቦርድ እንዲያቀርብ፣ ለወደፊቱ የኤክስፖርት አስተባባሪ ኮሚቴ ውሳኔም ሆነ አቅጣጫ ለአስፈጻሚ መ/ቤቶች የሚተላለፈው በጠቅላይ ሚኒስትር ጽ/ቤት በኩል ብቻ መሆኑን እናስታውቃለን::

ከሰላምታ ጋር

ደጠ አበራ

የጠቅላይ ሚኒስትር ጽ/ቤት ኃላፊ

ሚኒስትር

ግልባጭ:-

ለኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ቦርድ ጽ/ቤት

ለኢንዱስትሪ ሚኒስቴር

ለገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር

ለንግድ ሚኒስቴር

ለኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ

አዲስ አበባ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ The Federal Democratic Republic of Ethiopia
የጠቅላይ ሚኒስትር ጽ/ቤት Office of the Prime Minister